# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"...እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" ኢሳ 48÷17

God's Love, P.O.Box 6734, L.S. MO 64064.
E-mail mtizazu@hotmail.com -Fax/Ph 816 – 246-9395

ሰኔ 1994 JUNE 2002

**"ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ÷ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል ።" ኢሳ 54 ÷ 13**

## *"ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን?*

(ትንቢተ ኤርምያስ 45÷5)

መሻትህ ምንድን ነው? የምትሻውስ ለምንድን ነው? ተግተህ የምትፈልገው ነገር እግዚአብሔርን ያስከብራል? ወይስ የራስህን ጥቅምና ክብር ለማትረፍ ነው የምትፀልየው እግዚአብሔር የፈጠረህና ዳግመኛ ልደትን የሰጠህ ከእርሱ ጋር የቅርብ ወዳጅነት እንዲኖርህ ነው። ከሁሉ የሚበልጠውም እግዚአብሔር ለሰው ሊሰጥ የሚወደው ስጦታ ወዳጅነቱን ነው። እርሱን እንድታውቀው ራሱን ሊገልጽልህ ከሁሉ አብልጦ ይወዳል። ታላቅ ተብለው የሚገመቱ ስጦታዎችና በረከቶች ሁሉ ጊዜያዊ ናቸው። እርግጥ ነው፤ ጌታ ለዚህ ዓለም የሚሆኑ ስጦታዎች ሊሰጠን ይወዳል። ይህንን ማድረግ የሚወደው ግን ወደ ዕውነተኛውና ዘላለማዊው ስጦታ÷እርሱን ወደ ማወቅ ሊያደርሰን ባለው ዓላማ ነው።

ከእግዚአብሔር መሻትና መቀበል÷ጥሩ ወዳጅነትም ከእርሱ ጋር መፍጠር አስቸጋሪ አይደለም። የምንፈልገው እርሱን ከሆነ። እርሱን ሳይሆን ስጦታዎቹን የምንፈልግ ከሆነ ግን ምንኛ ጎስቋሎች ነን? አዘውትረህ የምትፀልየው ስለ ምንድን ነው? ይህን ስጠኝ÷ያንን ስጠኝ ነው? ወይስ ለጌታው እንደ ተሰጠ ሰው እርሱን ማወቅና ፈቃዱን ማድረግ ትመኛለህ? ክርስትናህን የምትመራው በራስህ ወይስ በጌታ ፍላጎት ነው? "እግዚአብሔርን አመልካለሁ÷ እንዳሰብሁት ግን ሰላምና ደስታ አላገኘሁም" ብለህ ታስባለህ? እፀልያለሁ÷የልቤ ግን አይፈጸምም ባይ ነህ? ቃሉ እንዲህ ይላል፦ "ትለምናላችሁ፤በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም።" (የያዕቆብ መልዕክት 4÷3)

ጌታ ኢየሱስ፡ በማቴዎስ ወንጌል 7÷7 "ለምኑ ይሰጣችሁማል፡ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፡ መዝጊያን አንኳኩ÷ ይከፈትላችሁማል" ብሏል። በእርግጥ የምንወደውን ሁሉ መለመን የተፈቀደ ነው። የምንወደው ሁሉ እግዚአብሔር የሚወደው መሆኑ ግን እንዴት ይታወቃል ብለን ብንጠይቅ መልሱ ቀላል ነው። ሰው ወደ እግዚአብሔር አብልጦ እየቀረበ ሲሄድ÷የቁሳቁስ ጥያቄው ዝርዝር እያጠረ ይሄዳል። "ስለዚህ (አሕዛብን) አትምሰሏቸው፡ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና" (ማቴዎስ 6÷8) እዚህ ላይ እንዲህ ከሆነ ለምን እንጸልያለን? ትል ይሆናል። በፀሎት ልምምድ ውስጥ እርሱን ወደ ማወቅ እንድንደርስ ነው።

"ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህ?" ጌታ ሆይ በመንፈስ ቅዱስ ሙላኝ ብለህ÷ወይም ተመሳሳይ ፀሎት ፀልየህ፡ሳይመለስልህ ቀርቶ ያውቃል? ምናልባት ራስህን በሙላት ለጌታ ኣላስረከብህም ይሆን? ምናልባት የምትፈልገው የራስህን ጥቅም ብቻ ይሆን? ለእግዚአብሔር ጨርሰህ ያላስረከብኸው ነገር ይኖር ይሆን? ከእግዚአብሔር የምትፈልገው ምን እንደሆነና ለምንስ እንደምትፈልገው ራስህን ለመመርመር ዝግጁ ነህ? ጌታ ልመናህን የዘጋብህ መስሎ ቢታይህ÷ የዘላለም ዕጣ ክፍልህን እንዳታበላሽ ነው። ከአጭሩ ምድራዊ ዘመንህ ይልቅ የዘላለም ዘመንህ አብልጦ ስለሚገደው ነው። "አባት ሆይ ÷ በእኔ እንዳለህ፡ እኔም በአንተ÷እነርሱ (ክርስቲያኖች) ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።" ተብሎ እንደ ተጻፈ፡ (የዮሐንስ ወንጌል 17÷21) እርሱ የሚያስብልህ ምን ያክል ታላቅ መሆኑን እንደማታውቅ ስለሚረዳ ነው። ( ከኦሰዋልድ ቼምበርስ መልዕክት የተተረጎመ)

# "አንበሳው"



አንበሳው የአራዊት ንጉሥ ነው ይባላል። ታድያ ከዕለታት አንድ ቀን በጫካው ውስጥ ሲንጎራደድ ስለ ራሱ ክብር ሃሳብ አደረበት። ሃሳቡም፦ አራዊት ሁሉ ንጉሥነቴን በእርግጥ ተቀብለው ይሆንን? የሚል ነበር። ይህንን በልቡ እያሰላሰለ ጫካ ለጫካ ሲዞር በድንገት ከጥንቸል ጋር ተገናኘ። እርሱም ፡ ጥንቸል ሆይ ፦ የአራዊት ንጉሥ ማን ነው? ሲል ጠየቃት። ጥንቸልም ሳታቅማማ ፦ ምን ይጠየቃል? አንተ ነሃ! አለችው። ከዚያም እልፍ ሲል መልከመልካሚን ፍጥረት ሚዳቆን አገኘና፡ አንቺ ሚዳቆ፦ የአራዊት ንጉሥ ማን ነው? አላት። እርሷም ክቡር አንበሳ! አንተ ነህ ብላ መለሰች። አንበሳም በደስታ መንገዱን ቀጠለ፤ ከዚያም መልካምና ሰማይ ጠቀስ ወደ ሆነው ወደ ጅራፍ መጣ። አንበሳም ይኸ ረዥም ፍጥረት ምናልባት ሌላ መልስ ይኖረው ይሆን? ብሎ አሰበና÷ ወደ ላይ አንጋጦ "ጅራፍ፦ ለአንተስ፡ የአራዊት ንጉሥ ማን ነው?" ሲል ጠየቀው። ቁመተ ተዥሙም ጅራፍ ከትክሻው ዝቅ በማለት÷ አንገቱን ደፍቶ÷ወደ አንበሳው ቀረበና÷ "አቶ አንበሳው፦ የሚተካከልህ የለም፤ አንተ ንጉሥ ነህ" አለው።

. አንበሳውም እኔ ወደር የሌለኝ ጀግናው÷ የሚል ይመስል እየተንጎራደደ መንገዱን ቀጠለ። ወድያውም አንድ ተንንቀሳቃሽ ተራራ የሚመስል÷ጆሮው ምንጣፍ መሰል÷ ኩምቢው አምስት ክንድ ከሚያክል ዝሆን ጋር ተገናኘ። ትንሽ ልቡ እንደ መፍራት ስላለበት÷ለማስደንገጥ ሲል÷ ድምጹን ጮክ አደረገና÷ "ዝሆን ፦ ለመሆኑ የአራዊት ንጉሥ ማን ነው?" ሲል ጠየቀው። ዝሆኑም ፦ አንዳች ሳይመልስ÷ ኩምቢውን ወደ ግራና ቀኝ እንደ ጅራፍ እያወናጨፈ÷ አንበሳውን መታው። ከዝያም በኩምቢው ጥምጥም አድርጎ አነሣውና፡ እንደ ወንጭፍ ወርውሮ፡ በአጠገቡ ከነበረው ተራራ ጋር አላተመው። አንበሳውም ራሱን አዞረው። ከወደቀበትም በቶሎ አልተነሣም። ከዚያም ቀስ ብሎ እየተንገዳገደ በ

እግሩ መቆም ቻለ። በመጨረሻም ወደ ዝሆኑ በትሕትና ቀ
ረብ አለና፥ “ጥያቄዬን መመለስ ባትችል እንዲህ መናደድ
ምን ያስፈልጋል?” ብሎት እያነከሰ ወደ ሠፈሩ ተመለሰ።

ይህ በአራዊት ባሕሪይ ተመስሎ የተነገረ ተረት ከሰው
ጋር እንዴት ይገናኝ ይሆን? ይህን መሰል ታሪክስ ሲነገር
የኖረው ለምን ይሆን?

እንደምናውቀው “አንበሳው” ከእግዚአብሔር የተሰጠ
ው ታላቅ ኃይል አለው። ከአራዊትም የሚደፍሩት ብዙ አ
ይደሉም። ይሁን እንጂ በተሰጠው ኃይልና ሥልጣን ተመ
ስገን ብሎ ከመርካት ፈንታ “ለመሆኑ የሚገዳደረኝ ይኖር
ይሆን?” የሚል ይመስል፥በልቡ ያደረው ሃሳብ አልጠቀመ
ውም። ይልቁንስ ታላቅ ውርደት አመጣበት።

የሰው ልጆችም እንደዚህ ያለ ስሕተት እናደርጋለን።
ይህንንም ታሪክ እንኳ የፈጠርነው (ሰዎች) ለራሳችን ትም
ሕርት ለመስጠት በማሰብ ነው። ስለዚህ እኛም የሰው ል
ጆች ያውም የእግዚአብሔር ሰዎች፥በልዩ ልዩ አቅጣጫዎ
ች መባረካችንን አይተን የምንስትበት ጊዜ አለ። በተቀበል
ነው፥ እኛ ለራሳችን ባልፈጠርነው ፀጋና ሥልጣን እንመካ
ለን። ወደ ትዕቢትም ሃሳብ እንገባለን። ተመልሶም ሊወሰ
ድብን የማይችል ይመስለናል። የትዕቢትንም መዘዝ እንዘ
ነጋለን።

የእግዚአብሔር ወዳጅ የሆነው፥ የምሥጉኑ የእስራኤል
ንጉሥ፥ የዳዊት ታርክ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። በመጽሐፈ
ሳሙኤል ካልዕ 23 የነገሩ አካሄድ ከተገለጸ በኋላ፥በምዕራፍ
24፥2 እንዲህ ይላል፦ “ንጉሡም ኢዮአብንና ከእርሱ ጋር
የነበሩትን የሠራዊት አለቆች፦ የሕዝቡን ድምር አውቅ ዘ
ንድ ከዳን ጀምሮ እስከ ቤርሳበረህ ድረስ ተመላለሱ፥ሕዝቡ
ንም ቁጠሩአቸው አላቸው።” ሕዝቡም ሁሉ ተቆጠሩ።
መሣሪያ ታጥቀው መዋጋት የሚችሉት ሰዎች ቁጥር ታወ
ቀ። እስራኤል ግን በዘመኑ ሁሉ ፥ በሠራዊት አምላክ በ
እግዚአብሔር ኃይል እንጂ፥በሰራዊት ብዛት በማሸነፍ አይ
ታወቅም። በዚህ ጊዜ ተሰወረበት እንጂ ንጉሡ ዳዊትም
ይህን አሳምሮ ያውቃል።

“አንበሳው” ባደረበት የሥልጣን ምዘና ሃሳብ ተነ
ሣስቶ በሚያዋርደው እጅ ወደቀ። በዳዊትም የሆነው
ተመሳሳይ ነገር ነው። ዳዊት ግን የእግዚአብሔር ሕ
ዝብ አስተዳዳሪ በመሆኑ፥ጥፋቱ ለብዙ ሰው ተረፈ።
ይህን አስመልክቶ ከአንበሳም ታሪክ ይልቅ፥የእግዚአ
ብሔር ቃል አረጋግጦ እንደሚያስተምረን፦ <u>“ትዕቢ
ት ከመጣች ውርደት ትመጣለች ፤ በትሑታን
ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች።”</u> (መጽሐፈ ምሳሌ 11፥2)
“የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት
ነው።” (መዝሙረ ዳዊት 111፥10) በፈርሐ እግዚአብሔር
ውስጥ ጌታ ይጠብቀን። አሜን።

*************************

# የወገኖቻችን ደብዳቤ

የእግዚአብሔርን ቃል ለማሰራጨት ስለምታደርጉት የ
ተሳካ ጥረት ጌታ ይባርካችሁ። በየካቲት እትማችሁ በ
ጣም ነው የተባረክሁት። ስለዚህም አፍሪቃ ካሉት ወገኖ
ች ... አንድ ሰው እስፖንሰር ለማድረግ፦ $15.00 ልከ
ናል። ጥሩዓለም እና ሚካኤል በለጠ (ዊስኮንስን)

---------------------------------------------------

እህት ነፃነት ረታ (ከሙዙሪ) በኬንያ ለሚኖሩ ወገኖች የ
ዓመት ደብዳቤ መላኪያ እስፖንሰርሽፕ $15.00 የረዳሽ
ን፦ ካለፈው ወር ጀምረን በተሰጠን አድራሻ መላክ ጀ
ምረናል። ----------------------------------------

-------ሰማይንና ምድርን የሠራ እግዚአብሔር ከፅዮን
ይባርክህ። መዝ 134፥3 ይህን መልዕክት ለምታዘጋጁ
የእግዚአብሔር ባርያዎች፥ በመጀመሪያ ከልብ የሆነ ሰ
ላምታዬን በአምላኬ ስም አቀርብላችኋለሁ። መልዕክ
ታችሁ ሁሌ ይደርሰኛል። ደግሞም እባረክበታለሁ።
ጌታ ይባርካችሁ። ባለፈው መልዕክታችሁ (ስለ እስፖ
ንሰር) የገንዘብ እርዳታ ነበረው። ግን ዛሬ ነገ ስል፥ (ዘ
ገየሁ)። በጣም ይቅርታ። በዕውነት ሳትታክቱ ስለም
ታደርጉት ጥረት ጌታ አብዝቶ ይባርካችሁ። በነገር ሁ
ሉ መከናወንን ይስጣችሁ። ሌላው ደግሞ (ባለፈው) መ
ልዕክታችሁ ስለትዳር የጻፋችሁት በጣም ልቤን ነክቶኛ
ል። ... ስለትዳር በዚህ መልኩ አይቼ አላውቅም ነበር፤
ጌታ ይባርካችሁ። እንግዲህ ጌታ ፀጋውን ባበዛልኝ መ
ጠን በፀሎቴ አስባችኋለሁ። (ከ$30.00 ርዳታ ጋር)
. ብሩክታዊት (ከሚነሶታ)

---------------------------------------------------

## እጅ ለእጅ ፥ ዓለም ለመድኃነዓለም

በጌታ ማሳ የዘራችሁትን በብዙ እጥፍ የሚያሰጭዳችሁ



ጌታ ታማኝ ነው።

**እስፖንሰር፦** ባለፉት ወራት በአፍሪቃ ላሉት ወገኖቻችን መልክታችንን ለመላክ (እስፖንሰሮች) እንደምንፈልግ አስታው
ቀን ነበር። በቶሎ እርዳታ የለገሳችሁን ጌታ በእጥፍ ይክፈላችሁ። እስከ አሁን ባገኘናቸው እርዳታዎች መላክ ጀምረናል። በአፍሪካ
ለሚኖር ሰው የማንበብ ጊዜው ብዙ ሲሆን የፖስታ ቴምቤር ዋጋ መክፈል ግን አይመቸውም። በሰሜን አሜሪካ ላለን ሰዎች ግን ከባድ
መስዋዕት ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ በኬንያ በስደት ለሚኖር አንድ ቤተሰብ መልክታችንን ዓመቱን ሙሉ ለመላክ <u>ከአሥራ አምስት
ዳለር ያነስ</u> ነው የሚፈጀው። *ለምታውቋቸው ወይም ለሚዛመዷችሁ፥ በአፍሪካ ሐገሮች ላሉ የአማርኛ አንባቢዎች፥
መልዕክታችንን ለማድረስ እስፖንሰር እንድታደርጉልን እንጠይቃችኋለን። የሰዎቹን ስምና አድራሻ ከመላኪያው
ገንዘብ ጋር ስትልኩልን ይህንኑ ለእነርሱም ማሳወቅ ትችላላችሁ። ኢየሱስ ጌታ ነው። ጌታ ይባርካችሁ።*

ባለፈው ወር፦ ቼክ ወይም money order (ለቴፕ ወይም ለርዳታ) ስትልኩልን M. Tizazu በሚል ስም እንድትልኩ የጠየቅ
ንበት ምክንያት ስለተወገደልን <u>ከዚህ በኋላ፥ በደብዳቤያችን ስም GOD'S LOVE ልትጽፉ ትችላላችሁ</u>። ማንኛውም
ለGOD'S LOVE (ከእግዚአብሔር ፍቅር) አገልግሎት የሚደረግ ስጦታ፦ የዩናይትድ ስቴትስ ታክስ ተቀናሽነት አለው።